# Joint Notice of Privacy Practices

Providence Health & Services

**የግል መረጃ አጠባበቅ ተግባራት ማስታወቂያ**

ይህ የጋራ የግል መረጃ አጠባበቅ ማስታወቂያ (Joint Notice of Privacy Practices) (ማስታወቂያ) እርስዎን የሚመለከት መረጃ፣ እንዴት  ጥቅም ላይ ሊውልና ለሌላ ሊሰጥ እንደሚችል፣ እንዲሁም እርስዎ መረጃውን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎን ተጠንቅቀው ያንብቡት። ይህ ማስታወቂያ የሚሰጥዎት፣ **Providence Health & Services** (**Providence**)፣ የሕክምና ባልደረቦችንና ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎችን (በዚህ ላይ በጥምሩ "እኛ" ወይም "የኛ" ተብለው የተጠቀሱትን) በመወከል ነው።

## ***Providence* *የእርስዎን የጤና መረጃ በምስጢር ለመጠበቅ ቃል ገብቷል***

ያለዎትን የተጠበቀ የጤና መረጃ (Protected Health Information) (በተለምዶ PHI ወይም የጤና መረጃ ተብሎ የሚጠራውን) ፣ በኤሌክትሮኒክ ፎርማት የቀረበውን PHI ን ጨምሮ፣ በምስጢር እንድንጠብቅ በሕግ ግዴታ አለብን። ያለዎትን የጤና መረጃ አስመልክቶ ስላሉብን ሕጋዊ ሐላፊነቶችና የግል መረጃ ጥበቃ ተግባራት ለእርሶ የማሳወቅና የዚህ ማስታወቂያ ተግባራትን ማክበር ይጠበቅብናል፣ ከእነዚህ የከረሩ ሕጎች ወይም መመሪያዎች ተፈጻሚ እስካልሆኑ ድረስ።  ይህ ማስታወቂያ የጤና እንክብካቤና አገልግሎቶችንና ፕሮግራሞችን ለእርስዎ የሚሰጡ ሁሉንም የ Providence ተቋሞችን ይመለከታል።

***ይህ ማስታወቂያ የሚመለከተው***

በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተገለጹት የግል መረጃ ጥበቃ ተግባራት፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በተግባር ይውላሉ፤

- ባሉን ቢሮዎች ውስጥ፣ እርስዎን የሚያክም ማንኛውም የጤና እንክብካቤ ባለሞያ።
- ሆስፒታሎችን፣ የቀዶ ጥገና ማእከሎችን፣ የቤት ውስጥ እንክብካቤን፣ ክሊኒኮችንና ሌሎች ተቋሞችን ጨምሮ፣ ሁሉም ተቋሞች፣ ቅርንጫፎችና ዩኒቶች።
- ሰራተኞች፣ የሕክምና ባልደረቦች፣ ሰልጣኞች፣ ተማሪዎች፣ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞችና ሌሎች በኛ ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ያሉ፣ በኛ የሚከፈላቸውም ሆኑ የማይከፈላቸውን የመሳሰሉትን ሁሉም የሥራ ኃይል (ዎርክፎርስ) አባሎች።
- በዚህ የግል መረጃ አጠባበቅ ተግባራት (Notice of Privacy Practices) ለመመራት የተስማሙ ሌሎች የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች።

ይህ ማስታወቂያ፣ በእርስዎ ፈቃድም ሆነ ያለ እርስዎ ፈቃድ፣ እንዲሁም ጤናዎን አስመልክቶ ሊኖርዎ ስለሚችሉ የተወሰኑ መብቶችን አስመልክቶ የሚኖሩ ተጨማሪ መረጃዎችን ጨምሮ፣ እርስዎን አስመልክቶ የሚኖሩ የጤና መረጃ ዝርዝር መረጃዎችን እንዴት አድርገን እንደምንጠቀምና እንደምንገልጽ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል።

## ***ያለ እርስዎ ፈቃድ ልንጠቀምበትና ለሌላ ልናካፍለው የምንችለው የጤና መረጃዎ***

**ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት፤**  ቀጠሮዎችን አስመልክቶ እንድናስታውስዎ፣ የምርመራ ውጤቶችን እንድንሰጥዎ፣ ስለሚኖሩ የሕክምና አማራጮች እንድንገልጽልዎ ወይም ስለሚኖሩ ሌሎች ከጤና ጋር ለሚዛመዱ እርዳታዎችና አገልግሎቶች እርሶን አግኝተን ማስታወሻ እንድንሰጥዎ፣ መረጃዎን ልንጠቀም እንችላለን።

**ሕክምና፤** የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለሚሰጥዎ ማንኛውም የጤና አገልግሎት ሰጪ፣ የእርስዎ መረጃ ሊሰጥ ይችላል። ይህም፣ የእርስዎን እንክብካቤ ከሌሎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ማቀናባበርንና ለሌሎች የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች መሸኛ መረጃ (ሪፈራል)መስጠት የመሳሰሉትን ሊያጠቃልል ይችላል። እርስዎን ለማከም የእርስዎ መረጃ የሚያስፈልጓቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ሐኪሞች፣ ፋርማሲስቶች፣ ነርሶችና ሌሎች እንደ ፊዚካል ቴራፒስት፣ የመኖሪያ ቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎችና የራጂ ቴክኒሻኖችን የሚሳሰሉትን ያጠቃልላሉ። አርስዎን በተቻለ መጠን ባስቸኳይ ለማከም እንዲቻል መረጃዎን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከሕክምና አገልግሎት ሰጪዎችዎ ጋር እንለዋወጣለን።

ለጤና ጥበቃዎ ለማገዝ ተሳታፊ ለሆኑ ማናቸውም የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞችዎ የጤና መረጃዎን ልናካፍል እንችላለን። ይህንን የምናደርገው ግን፣ እርስዎ ከተስማሙ ወይም የማይቃወሙ ከሆኑና፣ መረጃውን የምንሰጣቸው እርስዎን ለማገዝ የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ብቻ ነው። ይህንን የመሰለ መረጃ ለማካፈል መስማማት ወይም መቃወም ካልቻሉ፣ እኛ ባለን የፕሮፌሽናል ውሳኔ መሰረት፣ ለእርስዎ ጥቅም የተሻለ አማራጭ ነው ብለን በምንወስነው መሰረት፣ እንደ አስፈላጊነቱ የጤና እንክብካቤ መረጃዎችን እናካፍላለን። እርስዎ ከሞቱ በኋላ፣ የጤና እንክብካቤ መረጃ ለቤተሰብ አባል፣ ዘመድ ወይም በጤና እንክብካቤዎ ላይ ሚና ለሚጫወት ወይም ለሚኖሩ የጤና እንክብካቤ ቢሎች ክፍያ ለሚያደርግ ሌላ ሰው፣ ከዚህ በፊት አስቀድሞ ከተገለጸ ምርጫ ጋር የማይጻረር እስካልሆነ ድረስ፣ የጤና እንክብካቤ መረጃዎን እናካፍላለን።

**ክፍያ፤** ላገኟቸው የሕክምና አገልግሎቶች ክፍያ እንድናገኝ፣ የሕክምና መረጃዎችን ክፍያውን ለሚከፍሉ አካሎች መረጃዎን ልናካፍል እንችላለን። ይህም Medicare፣ Medicaid (በስቴቱ የቀረበ የጤና እቅድ) ወይም የመድን ዋስትና ኩባንያዎን ሊያጠቃልል ይችላል። የመድን ዋስትና ኩባንያዎ ወይም የጤና እቅድዎ፣ እንደ ለመድን ዋስትና ብቁነትዎን ለማወቅ፣ የተሰጥዎትን የጤና እንክብከቤ ምንኛ ያህል አስፈላጊ እንደነበረ ለመገምገም ወይም በሐኪም ቤት ውስጥ አገልግሎትን ለማግኘት ወይም ለመተኛት ፈቃድ ለመስጠት፣ ለመሳሰሉ ተግባሮች መረጃዎን ሊፈልግ ይችላል።

**የጤና እንክብካቤ ኦፐሬሽኖች፤** የሥራ ተባሮቻችንን ለመደገፍና ጥራቱን የጠበቀ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን እየሰጠን መኖናችንን ማረጋገጥ እንድንችል፣ የጤና እንክብካቤ መረጃዎን ልንጠቀም እንችላለን። ከነዚህ አንዳንድ ተግባራት ውስጥ፣ እንደ የጥራት ግምገማዎችን፣ የባልደረባ ወይም ሰራተኛ ግምገማን፣ የሕክምና ባልደረባ ስልጠናን፣ የንግድ ፈቃድ ማውጣትንና የሙያ ምስክር ወረቀት ማግኘትን፣ አሃዛዊ መረጃ መሰብሰብንና ባመራር ኤጀንሲዎች ለሚደረጉ ኦዲቶች የመሳሰሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

እንደ የጽሑፍ መረጃ ወይም የሂሳብ ክፍያ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ ሶስተኛ ወገኖች የእርሶን PHI ልናካፍል እንችላለን። በንደዚህ ጉዳዮች ላይ፣ የጤና እንክብካቤ መረጃዎችዎን፣ በሕግ ከተፈቀደላቸው መንገድ ውጭ፣ በሌላ መንገድ እንዳይጠቀሙ ወይም እንዳያካፍሉ፣ ከነዚህ ሶስተኛ ወገኖች ጋራ በጽሑፍ የተዘጋጁ ውሎች አሉን።

መረጃዎን (ስም፣ አድራሻ፣ የትውልድ ቀን፣ የአገልግሎት ዲፓርትመንት፣ አገልግሎት ሰጪ ሐኪም፣ የሕክምና ቀኖች፣ የሕክምና ውጤት) የገንዘብ እርዳታ መዋጮ ተግባሮች ልንጠቀምበት እንችላለን። **እንደነዚህ የመሳሰሉ መልእክቶች እንዳይደርሱዎት ምርጫ የማድረግ መብት አለዎት።** እንደነዚህ የመሰሉ መረጃዎችን ማግኘት የማይፈልጉ ከሆኑ፣ ከተራድኦ ድርጅት ቢሮዋችን ጋራ ይገናኙና እነዚህ መረጃዎች ወደ እርስዎ እንዳይላኩ ይጠይቁ።

እርስዎ እስካልተቃወሙ ድረስ፣ ስምዎና አድራሻዎ በታካሚ ስም ዝርዝር ላይ ይጨመራል። የሚጨመር ከሆነ፣ ስለ እርስዎ፣ በስምዎ ለሚጠይቅ ማንኛውም ሰው፣ በሆስፒታሉ ውስጥ የት እንደሚገኙና ስለ አጠቃላይ ሁኔታዎ፣ በጣም ውስን የሆነ መረጃ ብቻ እናካፍላለን። ሀይማኖትዎ ምን እንደ ሆነ ለመግለጽ ከመረጡና የማይቃወሙ ከሆኑ፣ ከእምነትዎ ወይም ከየሀይማኖትዎ ማህበረተሰብ ለሚመጡ የሀይማኖት መሪ፣ ስምዎንና የክፍል ቁጥርዎን ልንሰጥ እንችላለን።

ይህ ማስታወቂያ፣ በኛና በተወሰኑ ብቁ በሆኑ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎችና ድርጅቶች መሃል የሚደረግ የተደራጀ የጤና እንክብካቤ ውልንም (Organized Health Care Arrangement) ("OHCA") ይገልጻል። አንድ OHCA፣ የተለያዩ ሕጋዊ ሽፋን ያላቸው ወገኖች፣ ለጋራ ተግባር ዝግጅት፣ PHI እንዲጠቀሙና እንዲገልጹ ይፈቅዳል። የጤና እንክብካቤዎን ለማከናወን የሚያስችሉ አስፈላጊ የጤና መረጃን እርስ በእርስ ለመለዋወጥ ከተስማሙ የጤና እንክብካቤ ድርጅቶች ጋራ እንሳተፋለን። ለምሳሌ፣ የድንገተኛ እንክብካቤ አስፈልጎዎት ወደ ሐኪም ቤት ከገቡና፣ ጤንነትዎን አስመልክቶ አስፈላጊውን መረጃ መስጠት ካልቻሉ፣ OHCA የእርስዎን PHI፣ ካሉን የ OHCA ተሳታፊዎች ተጠቅመን እንድናክምዎ ያስችለናል። አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት፣ የእርሶን PHI ወዲያዉኑ ማግኘቱ፣ ለእርስዎ የተሻለ እንክብካቤ እንድንሰጥ ያስችለናል። የታካሚዎቻችንን የጤና መረጃ፣ በ OHCA ውስጥ ከሚሳተፉ ሌሎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ጋራ ባለን የጋራ የኤሌክትሮኒክ የጤና መዝገብ ውስጥ እናስቀምጠዋለን። Providence እና የ OHCA አባሎች፣ ለሕክምና፣ ለክፍያና ለጤና እንክብካቤ ጉዳዮች፣ የእርስዎን መረጃ በቀላሉ መለዋወጥ መቻል ይኖርባቸዋል። በዚህ ምክንያት፣ የ OHCA እና ይህንን የጋራ ማስታወቂያ አውጥተናል። የ OHCA አባሎች የራሳቸውን ማስታወቂያ(ዎች) ለማውጣት ምርጫ ማድረግ ይችላሉ። በእኛ OHCA ውስጥ ስለሚሳተፉ ድርጅቶች መረጃ ለማግኘት፣ በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተጠቀሰውን የ OHCA Privacy Office ያነጋግሩ።

***<u>ያለ እርስዎ ፈቃድ</u> ልንጠቀምባቸውና ልናካፍላቸው የምንችል መረጃዎች***

የጤና መረጃዎች ያለ እርስዎ ፈቃድ ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ሊሰራጩ የሚችሉበት አያሌ መንገዶች አሉ። በአጠቃላዩ፣ እነዚህ ተግባሮች ወይም ስርጭቶች በሕግ የግድ መፈጸም ያለባቸው ናቸው ወይም ደግሞ ለሕዝብ ጤናና ደህንነት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ናቸው።

**ሕግ የሚያስገድድ ሲሆን፤** ሕግ ካስገደደን፣ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም ልናካፍል እንችላለን። ይህ ከተፈጸመ፣ ሕጉ የጠየቀንን እንፈጽማለን፣ እንዲሁም የምናካፍለው አስፈላጊውን መረጃ ብቻ ነው።

**የማሕበራዊ ጤና፤** የጤና መረጃዎን፣ ለማሕበራዊ ጤና ተግባራት ለሕዝብ የጤና ባለስልጣኖች ልንሰጥ እንችላለን። የማሕበራዊ የጤና ተግባሮች እንደ በሽታን፣ ጉዳትን፣ የአካል መታጎልን መከላከልንና መቆጣጠርን፣ እንዲሁም ለጉስቁልና፣ ለቸልተኝነት ወይም ለቤተሰብ ብጥብጥ ዘገባዎች ምላሽ ማድረግ የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ። የጤና መረጃዎን፣ ከፉኛ ሁኔታዎችን፣ የምርት ውጤት ብልሽቶችን ወይም ችግሮችን፣ የባዮሎጂ የምርት ውጤቶች ብልሽቶችን፣ ወይም የምርቶች ውጤቶችን ወደ ፋብሪካ ለመመለስ፣ ለመጠገን ወይም በሌላ እንዲተኩ ለማድረግ፣ ሪፖርት ማድረግ ላለባቸው፣ ግለሰቦች ወይም ኤጀንሲዎች መግለጽ ሊኖርብን ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ የመረጃ ስርጭት፣ ያሉትን የስቴትና የፌደራል ሕጎችን የተከተለ ይሆናል።

**የጤና ተቆጣጣሪዎች፤** የጤና መረጃዎችዎን፣ እንደ ኦዲቶች፣ ምርመራዎችና ቁጥጥሮች የመሳሰሉትን፣ በሕግ እንዲቆጣጠሩ ፈቃድ ለተሰጣቸው የጤና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ልንሰጥ እንችላለን። የጤና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች፣ የጤና እንክብካቤ ሥርዓትን፣ የመንግስት እርዳታ ፕሮግራሞችን፣ የመንግስት የመቆጣጠሪያ ፕሮግራሞችንና ሕዝባዊ መብቶችን የሚያስተዳድሩ የመንግስት ኤጀንሲዎች የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ።

**ሕጋዊ አፈጻጸም፤** በአንድ የአስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ አፈጻጸም ወይም ለፍርድ ቤት መጥሪያ (ሰፒና)፣ የዳሰሳ (ዲስካቨሪ) ጥያቄ ወይም ሌላ ሕጋዊ ሂደት የፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ትእዛዝ ምላሽ ለመስጠት፣ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም ወይም ልናካፍል እንችላለን።

**ሕግን ለማስከበር፤** የጤና መረጃዎን ለሕግ ማስከበሪያ ተግባሮች ልንጠቀምበት ወይም ልንሰጥ እንችላለን። ምሳሌዎቹ የሚያጠቃልሉት (1) ለሕጋዊ ሒደቶች ምላሽ ለመስጠት፣ (2) አንድን ተጠርጣሪ ለይቶ ለማወቅ ወይም የት እንዳለ ለማወቅ የተወሰነ መረጃ መስጠት፣ (3) ስለ ወንጀል ተጠቂዎች መረጃ መስጠት፣ (4) በተፈጸመ የወንጀል ስራ ምክንያት የሞት ጥርጣሬን ማሳወቅ፣ (5) በቅጥር ግቢያችን ውስጥ የተፈጸመ ወንጀልን ሪፖርት ማድረግ፣ እንዲሁም (6) ለድንግተኛ ሕክምና፣ ወንጀል እንድተፈጸመ የተጠረጠረበትን ቦታ ማሳወቅ።

**አንድ በጣም አስጊ ሁኔታ እንዳይከሰት ለመከላከል፤** ይህን መረጃ መጠቀሙ የአንድን ሰው ወይም ህዝብን የጤና ወይም የደህንነት ሁኔታ፣ ከጹኑና ሊከሰት ከሚችል አደጋ ሊያድን ወይም ሊያቃልል ያስችላል ብለን፣ በቀና ልባችን ካመንንበት፣ የጤና መረጃዎችዎን ልንጠቀምበት ወይም ልንሰጥ እንችላለን። መረጃው የሚሰጠው፣ አደጋውን ሊያስወግድ ወይም ሊያቃልል ይችላል ተብሎ ለታመነበት ሰው ብቻ ነው።

**የሟችን አሟሟት የሚያጠኑ ባለሞያዎች (ኮረነርስ)፣ የቀብር ዳይሬክተሮችና የሰውነት ክፍል ልገሳ (ኦርጋን ዶኔሽን)፤** መረጃዎን፣ ማንነትን ለማወቂያ ተግባሮች፣ የሞት ምክንያትን ለይቶ ለማወቅ ወይም ለሌሎች በሕግ ለሚያስፈልጉ ተግባሮች፣ የሟችን አሟሟት ለሚያጠና ባለሞያ (ኮረነር) ወይም የሕክምና መርማሪ ልንሰጥ እንችላለን። አንድ የቀብር ዳይሬክተር ስራውን/ዋን መስራት እንዲችል/ድትችል፣ የጤና መረጃዎን ልንሰጥ እንችላለን። የሰውነት ሆድ እቃ (ኦርጋን)፣ ዓይን ወይም የቲሹ ልገሳን ለማከናወን የሚያስችል መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።

**ምርምር፤** የጤና መረጃዎችዎን፣ በ Institutional Review Board እና/ወይም Privacy Board ፈቃድ እስከ ተሰጠው ድረስና ግላዊነትዎን ለመጠበቅ የሚያስችሉ የምርምር ፕሮቶኮሎች ፈቃድ እስከተሰጣቸው ድረስ፣ ለተመራማሪዎች ልንሰጥ እንችላለን። የምርምር ፕሮጀክት ለመፈጸም ዝግጅት ላይ ላሉ ሰዎች፣ ስለ እርስዎ የጤና እንክብካቤ መረጃ ልንሰጣቸው እንችላለን።

**የውትድርና ተግባር እና ብሔራዊ ደህንነት፤** የጤና መረጃዎችን ለሚከተሉት ምክንያቶች ለመከላከያ ሐይል ባልደረቦች ልንሰጥ እንችላለን፤ (1) በሚመለከተው የመከላከያ ሐይል አመራር ባለስልጣን አስፈላጊ ነው ለተባለ ተግባር፣ (2) በ Department of Veterans Affairs ለእርዳታ ብቁነትዎን ማወቂያ ተግባሮች፣ ወይም (3) በውጭ ሀገር የሚገኝ የውትድርና ባለሥልጣን አባል ከሆኑ፣ ለዚህ የውጭ ሀገር የውትድርና ባለሥልጣን። የጤና መረጃዎን፣ እንደ ለፕረዚደንቱ የጥበቃ አገልግሎቶችን ወይም ሌላ መረጃን ለመቀበል ስልጣን የተሰጠውን አካል ጨምሮ፣ ብሔራዊ ደህንነትና የኢንተሊጀንስ ተግባሮችን ለማከናወን ፈቃድ ለተሰጠው የፌደራላዊ ባለሥልጣን፣ ልንሰጥ እንችላለን።

**የወህኒ ቤት ተቀማጮች/ታሳሪዎች፤** በአንድ የማረምያ ተቋም ውስጥ እስረኛ ወይም በጥበቃ ላይ ከሆነና፣ እርስዎን ለማከም ወይም የእርስዎን፣ የሌላ እስረኞችን፣ እንዲሁም የማረሚያ ተቋሙን ሰራተኞችን ወይንም የሌሎችን ጤናና ደህንነትን ለመጠበቅ መረጃው የሚፈለግ ከሆነ፣ የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀምበት ወይም ለማረምያ ተቋሙ ወይም ለሕግ አስከባሪ ባለ ስልጣን ልንሰጥ እንችላለን።

**የሰራተኞች ካሳ (ዎርከርስ ኮምፐንሴሽን)፤** የጤና መረጃዎን እንደ አስፈላጊነቱ፣ የሰራተኛ ካሳ ሕጎችና ሌሎች ተመሳሳይ በሕግ የተመሰረቱ ፕሮግራሞችን ትእዛዝ ለማክበር፣ ልንጠቀምበት ወይም ልንሰጥ እንችላለን።

**ለደረሰ አደጋ እርዳታ፤** ቤተሰብዎና ጓደኞችዎ ስለ ሁኔታዎ፣ ደህንነትዎና ያሉበት ቦታ ይነገራቸው ዘንድ፣ ለደረሰው አደጋ እርዳታ በመስጠት ለሚረዳው ክፍል፣ የጤና እንክብካቤ መረጃዎን ልንሰጣቸው እንችላለን።

***የእርስዎን <u>ፈቃድ ጠይቀን</u> የጤና መረጃዎችን ልንጠቀምበትና ልንሰጥ የምንችልባቸው መንገዶች***

እንደ ለገበያ ሽያጭ ማስተዋወቅ፣ የጤና መረጃን መሸጥ ወይም የሳይኮቴራፒ ማሳሰቢያዎች መስጠትን የሚያካትቱ አንዳንድ የጤና መረጃዎችዎ ጥቅሞችና መግለጫዎች በእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ብቻ ይደረጋሉ። በሰጡን ፈቃድ መሰረት እስካሁን ድረስ የወሰድናቸውን እርምጃዎችን ሳይጨምር፣ ይህንን ፈቃድ፣ በማንኛውም ግዜ በጽሑፍ መሻር ይችላሉ።

በዚህ ማስታወቂያ ላይ ያልተገለጹ አጠቃቀሞችና መግለጫዎች፣ ከእርስዎ በጽሑፍ በተገኘ ፈቃድ ብቻ ይፈጸማሉ።

የፌደራልና የስቴት ሕጎች፣ ለጎጂ ዕጽ ወይም ለአልኮል ሱስን ሕክምና ፕሮግራሞች፣ በግብረስጋ ለሚተላለፉ በሽታዎች ወይም ለአእምሮ ጤና ሕክምና ፕሮግራሞች ተብሎ ሊሰጥ የሚችለው የጤና መረጃዎ ላይ ተጨማሪ ገደቦችን ሊያደርጉ ይችላሉ።

***መብቶችዎ***

**ገደቦች እንዲደረጉ የመጠየቅ መብት፤** ለሕክምና፣ ለክፍያ፣ ወይም ለጤና እንክብካቤ ስራዎች፣ የእርስዎን የጤና መረጃ እንዴት ልንጠቀምበት ወይም ልናሰራጭ እንደምንችል ገደብ እንድናደርግ የመጠየቅ መብት አለዎት። ያቀረቡትን ጥያቄ ግምት ውስጥ እናስገባዋለን፣ ቢሆንም ባቀረቧቸው ገደቦች (ከታች ከተጠቀሱት በቀር) የመስማማት ግዴታ የለብንም። ገደብ እንዲደረግ ከተስማማን፣ በድንገተኛ ሁኔታ ላይ ካልሆነ በቀር፣ የተመሰረተውን ገደብ ጥሰን፣ የእርስዎን የጤና መረጃ አንጠቀምም ወይም አናሰራጭም። ገደቡ ካሁን በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ፣ እናሳውቅዎታለን።

**ለጤና የመድን ዋስትና መረጃን ለመገደብ ያለዎት መብት፤** አገልግሎቱን በሚያገኙበት ወቅት፣ ከኪስዎ ሙሉ በሙሉ ለከፈሉባቸው እቃዎች ወይም አገልግሎቶች መረጃን ለመድን ዋስትናዎች እንዳንገልጽ፣ በጽሑፍ ሊጠይቁ ይችላሉ። የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ይህንን መረጃ ለጤና የመድን ዋስትናዎችዎ ላለመግለጽ መስማማት ይኖርብናል።

**በምስጢር የሚደረጉ ግንኙነቶች፤** የጤና መረጃዎን አስመልክቶ በተለዩ መንገዶች ወይም በሌላ አማራጭ ቦታዎች ላይ ከእርስዎ ጋር ሀሳብ ለመለዋወጥ ወይም ለመግባባት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች፣ እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ፍላጎትዎን ለማሟላት እንሞክራለን። ለምሳሌ፣ በአንድ የሕክምና የመድን ዋስትና ውስጥ ሽፋን ካለዎ፣ ግን ዋና ተመዝጋቢው እርስዎ ካልሆኑና፣ መረጃዎን ከዋና ተመዝጋቢው አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ እንዲላክልዎ ከጠየቁን፣ አብዛኛውን ግዜ እናደርግልዎታለን።

**ያለ አግባብ ጥቅም ላይ ከዋለ ለእርስዎ ስለ ማሳወቅ፤** የጤና መረጃዎ ያለ አግባብ ጥቅም ላይ ከዋለ፣ ሕግ በሚጠይቀው መሰረት፣ ማስታወቂያ የማግኘት መብት አለዎት።

**የጤና መረጃዎን ማግኘትን በሚመለከት፤** እኛ የምናስተዳድረውን የጤና መረጃዎን ግልባጮች፣ የማግኘት መብት አለዎት፣ ግን የሆኑ ጥቂት ገደቦች ይኖራሉ። መረጃዎን ለማግኘት በጽሑፍ መጠየቅ ይችላሉ፣ እኒሁም የመረጃዎን ግልባጭ በኤሌክትሮኒክ ፎርማት እንዲሰጥዎ መጠየቅ ደግሞ ይችላሉ። የጤና መረጃዎችን አዘጋጅተን ለእርስዎ ለማቅረብ ላወጣነው ወጪ እርስዎን የማስከፈል መብት ይኖረናል። የጤና መረጃዎች ወደ እንደ ሌላ ሐኪም፣ እንክብካቤ ሰጪ ወይም የኦንላይን የግል የጤና መዝገብ ለመሳሰሉት፣ እንዲላክልዎ የመጠየቅ መብት አለዎት።

**የጤና መረጃዎን አስመልክቶ የሚኖሩ መሻሻሎች፤** የጤና መረጃዎን ማንኛውም ክፍል እንዲሻሻል የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህን የጠየቁትን ማሻሻያ፣ በጽሑፍ አዘጋጅተው ለአገልግሎት መስጪያው የሕክምና መዝገቦች ክፍል ማቅረብ ይኖርብዎታል። በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ያቀረቡትን ጥያቄ ላንቀበለው እንችላለን፣ ይህ የጤና መረጃዎች በሌላ አገልግሎት ሰጪ መቼ ተዘጋጅቶ እንደነበረ ወይም መረጃዎ ትክክልና የተሟላ ነው ብለን ካመንበት። ጥያቄዎን ውድቅ የምናደርግበት ማንኛውም እርምጃ በጽሑፍ ይሆናል። ጥያቄዎን ውድቅ ያደርግንበትን እርምጃ፣ በጽሑፍ በተዘጋጀ የተቃውሞ ደብዳቤ አድርገው ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

**ለሌላ ወገን የተሰጡ መረጃዎችን ማሳወቅን አስመልክቶ፤** ለሕክምና፣ ለክፍያ፣ ወይም ለጤና እንክብካቤ ስራዎች፣ ወይም በሰጡት ፈቃድ መሰረት የተሰራጩ መረጃዎችን ሳይጨምር፣ ለምናሰራጫቸው የጤና መረጃዎችዎ ዝርዝሮችን የማወቅ መብት አለዎት። በአንድ የስርጭት ዝርዝር ላይ በተለምዶ የሚኖሩት፣ ለማሕበራዊ ጤና ተግባሮች፣ ለሕግ ማስከበሪያ ተግባር፣ ለሕግ አፈጻጸም፣ ወይም እንደ ለልደትና ለሞት ምክር ወረቀት ለመሰሉት ሌሎች አስፈላጊ ማስታወቂያዎች ይሆናሉ።

**መብቶችዎን መጠቀም፤** ከላይ የተጠቀሱትን መብቶችዎን ለመጠቀም ወይም ከላይ ከተጠቀሱት ተግባሮች በተለይ ለሌላ ተግባር፣ የጤና መረጃዎን ሌላ ሰው ለማካፈል ከፈለጉ፣ ተገቢውን የሕክምና መዝገብ ክፍል ያነጋግሩ።

***ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች***

ጥያቄ ካለዎት ወይም ማናቸውም የግላዊ መብቶችዎ እንደተጣሱ የሚያሳስብዎት ከሆነ፣ የ Privacy Officer በ **1-800-510-3375** ይደውሉ። ለ Secretary of Health and Human Services ከዚህ በታች በተጠቀሱት አድራሻዎች ቅሬታዎን የማሰማት መብትም አለዎት፤

**Office for Civil Rights – AK, WA, OR, MT**
U.S. Department of Health and Human Services
2201 Sixth Avenue - M/S: RX-11
Seattle, WA 98121-1831

**Office for Civil Rights – CA**
U.S. Department of Health and Human Services
90 7th Street, Suite 4-100
San Francisco, CA 94103
የቅሬታ ማመልከቻ በማስገባትዎ ምክንያት የብቀላ እርምጃ አይደርስብዎትም።

**የጋራ የግል መረጃ አጠባበቅ ተግባራት ማስታወቂያ ለውጦች**

በማስታወቂያችን ላይ ያሉትን ውሎች በማንኛውም ግዜ ላይ የመቀየር መብት አለን። በማስታወቂያው ላይ የሚኖሩ አዲስ ውሎች፣ እኛ በምናስተዳድራቸው የተጠበቁ የጤና መረጃ መረጃዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ። ወቅታዊ የሆነውን የማስታወቂያችንን ግልባጭ በዌብሳይታችን **www.providence.org** መመልከት፣ ወይም ከሕክምና መዝገቦች ክፍል፣ የግል መረጃ ሹም፣ ወይም ከምዝገባ ባልደረባ በማንኛውም ግዜ ላይ መጠየቅ ይችላሉ።